አፍሪካ ቲቪ

1

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች

5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ሸሪዓዊ ሩቅያዎች (መንፈሳዊ ህክምና) አደራረግ

- (ከሸሪዓ ጋር ግጭት የሌላቸው መንፈሳዊ የሕክምና ስልቶች)
- የአሏህ ﷻ ተፈጥሮዓዊ ክንውንን በጥልቀት ያስተዋለ ሰው ፈተና አሏህ በሰዎች ህይዎት ላይ ያስተላለፈው ነባራዊ ውሳኔ መሆኑን በትክክል ይረዳል፡፡
- አላህ (ﷻ) እንዲህ አለ:- (ሙሐመድ ሆይ ከፍርሃትና ከርሀብም በጥቂት ነገር፤ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በዕርግጥ እንሞክራችኋለን፡ ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡) (አል በቀራ፤155)
- መልካም ሰዎች በላእ (መከራ) እና ችግር አይደርስባቸውም የሚል ሰው ፈፅሞ ተሳስቷል፡፡ እንዲያውም መፈተን ከኢማን (እምነት) ምልክቶች ነው፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ:- “ከሰዎች ሁሉ ፈተና የሚበዛባቸው እነማን ናቸው ተብለው ተጠይቀው፡- ነቢያት፤ ከዚያም ሷሊሆች፤ ከዚያም (በኢማን) የተሻሉት ከነሱ የሚጠጉት (የተሻሉት)...” ሲሉ መልሰዋል፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ የሚፈተነው በእምነቱ ልክ ነው፡፡
- በእምነቱ ጠንከር ያለ ከሆነ ፈተናውም እንደዚያው ይበዛበታል፡፡
- በእምነቱ ደከም ያለ ከሆነ ፈተናውም ይቀንሳል ብለዋል፡፡
- ፈተና አላህ (ﷻ) ባሪያውን የመውደዱ ምልክትም ነው፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ (አላህ የተወሰኑ ሰዎችን ሲወድ ይፈትናቸዋል (ይሞክራቸዋል))፡፡
- ፈተና አላህ (ﷻ) ለባሮቹ ኸይር መሻቱን ከሚያመለክቱት አያሌ ነገሮች አንዱም ነው፡፡

1

- ነቢዩ ﷺ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ (አላህ ለባሪያው ኸይር ሲያስብ ቅጥቱን በዚህች ዐለም ያፋጥንለታል፡፡ መጥፎ ሲያስብበት ደግሞ ከነወንጀሉ ዝም ይለውና ቅጣቱን ለዚያኛው ዐለም ያዘገይለታል፡፡) ብለዋል፡፡ ቢያንስም ፈተና ለወንጀል ማሳበሻ ነው፡፡

- ነብዩ ﷺ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በእሾህም ሆነ ከዚያ በላይ በሚያጋጥመው ችግር ለሙስሊም ዛፍ ቅጠሏን እንደምታራግፍ ሁሉ ወንጀሉን የሚያራግፍለት ቢሆን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡) ብለዋል፡፡

- ስለዚህ የተፈተነው ሙስሊም ጠንካራ ከሆነ ላለፉት ወንጀሎቹ ማሳረፘ ወይም ለደረጃ እድገቱ ምክንያት ናቸው፡፡ ወንጀለኛ ከሆነ ግን ለወንጀሉ ማሰረዣና አደገኝነቷን መግለጫ ናቸው፡፡

- አላህ (ﷻ) እንዲህ ይላል፡- (የሰዎች እጆች በሰሩት ኃጢአት ምክንያት
የዚያን የሰሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና
 በባህር ተገለጠ (ተሰራጨ))፡፡ ብሏል፡፡

- **የፈተና ዓይነቶች** ብዙ ናቸው፡፡

(1) በኸይር መፈተን ማለትም ለምሳሌ ገንዘብን በማብዛት መፈተን አለ፤

(2) በመጥፎ ነገሮች ማለትም በፍርሃት፤ በረሃብ በድህነት መፈተንም አለ፡፡

- አላህ (ﷻ) ‘‘በኸይርና በሸር እንፈትናችኋለን ወደኛም ትመለሣላችሁ’’
- መነሻቸው ከምቀኝነት የሆኑት ድግምትና አይነናስ (የሰው ዐይን) እንዲሁ መታመምና መሞትም ከፈተና ነው፡፡
- ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ አቡዳውድ ጦይሊሲ በዘገቡት ሐዲስ
  (ከህዝቦቼ ብዙዎች የሚሞቱት ከአላህ ውሳኔ በኋላ በአይነናስ
  (በሰው አይን)ነው፡፡) ብለዋል፡፡